# ሲ.አይ.ኤ፤ ልጆቹና የልጅልጆቹ ሴራ በኢትዮጵያ

ጌታቸው ረዳ

(የኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ)

መስከረም-2006

www.ethiopiansemay.blogspot.com getachre@aiol.com

ላለፈው 21 አመታት ወያኔና ሻዕቢያ የተባሉ ከትግራይ ክ/ሐገር እና ከኤርትራ ክ/ሐገር የበቀሉ ሲ.አይ.ኤ. የተባለው የአሜሪካ የስለላ ድርጅት ተንከባክቦ ለስልጣን ያበቃቸው አገር በቀል ሽምጥ ተዋጊ ሃይሎች ወደ መንበረ ስልጣን ከወጡ በኋላ በሕዝብ ላይ ያደረሱትና አሁንም እያደረሱት ያለውን መከራ፤ የማስተዋል ሕሊና ላለው ሰው የተሰወረ ድርጊት አይደለም። እንደዚህ ያለው የሕዘብ መከራና ጦርነት፤ ፍትሕ ማጣትና አድለዎ፤ስደትና ሞት፤መደፈርና መዋረድ፤የማንነት ማጣት፤የራስ ፍለጋና ጎሰኝነትና የጽንፈኛ ሃይማኖት አክራሪነት፤ በኢትዮጵያና ኤርትራ ሕዝብ እንዲከሰት ያጠነጠኑት ሴራ እነማን እንደሆኑ በዝርዝርና በፎቶ ግራፍ የተደገፈ ሰነድ እንመለከታለን። ዛሬም የነሱን ኮቴ በመከተል የውጭ አገር ስለላ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ጠላቶች እንክብካቤ እያደረጉላቸው በፖለቲካ መድረግ ብቅ እያሉ መድረኩንና የሕዝቡን ሕሊና በመጥለፍና በማጃጃል የሚገኙና፤ እንዲሁም አድፍጠው ጊዜ ሲያመች ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ ለማለት ያደፈጡ ትምህርታቸውን/ስልጠናቸውን በመከታተል ላይ ያሉ እንዲሁም በህ.ወ.ሓ.ትና ሻዕቢያ ድርጅቶች ውስጥም ከፍተኛ የአመራር ቦታ የነበራቸው ከመለስና ከኢሳያስ ጋር ተጋጭተው ስልጣናቸውን ለቀው በተባበሩት መንግሥታት እና ዓለም ዐቀፍ ሰናይ ድርጅቶች

ወይንም በግል ንግድ የተሰማሩ አድፍጠው ክፍትት ሲፈጠር ብቅ ለማለት የተዘጋጁ የስለላው ድርጅት የSeed Plantation Project" "የተከላ ፕሮጀክት" ፍሬዎች በብዛት እየተፈለፈሉ እንደሆነ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በንቃት መከታተል እንዳለብን እመክራለሁ።

ለብዙ ዘመናት ኢትዮጵያዊያን ውስጥ እየታየ ያለ ችግር ፖለቲካውን የአለማወቅ ብቻ ሳይሆን ጉዳት ላይ የደረሰን፤ ባንዳዎችና ስራቸው ለይተን ባለመከታተላችንም ጭምር ነው። አርበኞችን ብቻ ስናሞግስ በተጻራሪ የቆሙት "ባንዳዎችን" ሳናጋልጥ በእውር እርምጃ ስንደናበር ለባንዳዎች መጫወቻ ሜዳ በሰፊው በመለቀቁ ፤ አገሪቱና ሕዝቡ ችግር ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል። ይህ ጨዋታ ከጣሊያን በኋላ በንጉሡ ጊዜ የጀመረ ጅላጅልነት አሁንም እየተደገመ ነውና በዚህ ለማተኮር እወዳለሁ። ይህ ጅላጀልነትን ማቆምና መጠቆም ለትግሉ ወሳኝና ዓይነተኛ የትግሉ ፈር መሆኑን መገለጽ ጠቃሚነት አለው ። ከ21 አመት በኋላ ምን ተማርን? የሚለው መልስ በትክከል መለሱን ያገኘነው አይመስልም።።

በኤርትራ እንጀምር። በትግርኛ ህ.ግ.ሓ.ኤ./ብሎ ራሱን የሰየመ ምዕራባዊ ቆላና መሰል እስላማዊ ቡድኖች በመጀመሪያ "ጀብሃ" ከዚያም "ሻዕቢያ" በማለት ዓረብኛ በሚጽፉና በሚናገሩ ዓረብ አምላኪ ቡድኖች የሰየሙት ዓረቦችና ሲ.አይ.ኤ የመለመሉት የኤርትራው ቅጥረኛ ቡድን በኢሳያስ አፈወርቂ ቢያንስ ለ50 ዓመት

በላይ ሲመራ፤ በመለስ ዜናዊ የተመራው ህወሓት/ተሓሕት ብሎ ራሱን የሰየመው ተገንጣይ ቡድን ደግሞ የራሱን "ትግራይ ሪፑብሊክ" አገር ለመመስረት ሰራሽ ባንዴራ ፈጥረው ሁለቱም ቅጥረኞች የየበኩላቸው አገርንና ሕዝብን በማፈረስ በአፍራሽ ሴራና ጥቃት በሰፊው ተሳትፈዋል።

ሁለቱም የኤርትራና የትግራይ ሕዝብ ሕሊና ለመንጠቅ እንዲያመቻቸው የሕዝቡን ስሜት በተገንጣይነትና በባዕድነት አሰልፈው ተዋጊዎቻቸውና ተከታዮቻቸው በጭፈራና ጣዕም ባላቸው ዜማዎችና መዝሙሮች እየነተቱ በፖለቲካቸው ዙርያ ለማሰለፍ በቅተዋል። የትግላቸው መነሻ ከሚገባ በላይ በጣም በመለጠጥ ፈሩን በማስካድ ፤ ልክ ጀርመኖች በሂትለር መሪነት በባደረጉት የተሳሳተ ስሜት በሁለቱም ሕዝብ በኩል አማራ/ኢትዮጵያ የተባለ የጋራ ማዕከላዊ ጠላታችን ብለው እንዲወስዱ ጣሊያኖች የቀየሱት አበጣባጭ ስሜት ተግባራዊ አድርገዋል።

"ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራም ሆነ ህዝባዊ ሓርነት ትግራይ" ለዓረቦች፤ ለአሜሪካኖችና ለእስራሎች ስትራተጂካዊ/ጠቀሜታ ተብለው እንደተቦኩ አያጠራጥርም። የኤርትራም ሆነ የትግራይ ሕዝብ የኢሰያስም፤የመለስ ዜናዊም ሆነ የሲ.ኣይ.ኤ ውጥን ሴራ ሳያስተውል "ደርግ" ባደረሰው ጭፍጨፋም ሆነ "አማራ" ጠላትህ ነው በማለት የነበረው ሡራዊት በአማራነትና በደርግነት በማያያዝ "ነጻነት/አርነት" የሚል ማዘናጊያ/ማጃጃያ ጥዑም ምኞት

ለማምጣት በማትኮር ያለውን ሃይል፤ንብረትና መስዋዕትንት ለሁለቱም ቅጥረኞች በመለገስ በሲ.አይ.ኤና በዓረቦች ዕርዳታ እየታገዙ የተቦካው የእርሾ ሴራ በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም እውን ሆኖ፤ ሕዝቡ ላልጠበቀው ድቅድቅ ጨለማ ተዳርጓል።

የኤርትራም ሆነ የትግራይ ቡድን ባብዛኛው አገልግሎታቸው ያበረከቱት ለሞሳዶች፤ለሲ.አይ.ኤ እና ለአረቦች አንደሆነ ከተደረጉት ክንዋኔዎች ግልፅ ያደርጉልናል። ኢትዮጵያ የሲአይኤ/የሞሳዶችና የዓረቦች መገልገያ መሬት ብቻ ሳትሆን ቻይና የተባለው አገርም ኢትዮጵያን ከተጠቀሱት ጋር በእኩል ምናልባትም የበለጠ የመቀራመት ዕድል በማግኘቱ ድቅቅ ያሉ "ሙጩጩ ዓይን" እና ጨፍራራ ጸጉረ ዞማ ያለቸው በርካታ የቻይና ዲቃላዎች በምድሪቱ ላይ እየተወለዱ ሲሆኑ፡ ሕንዶችም ሳዮናና ጭፈራቸው ባዳዲስ የኪነት ሰዎች እየተዘፈነ ለም መሬቶች እያረሱ የተራበው ሕዝባቸውን በመመገብ ላይ ይገኛሉ። የምስራቅ አፍሪካው የሲ.አይ.ኤ ስለላ ክፍል ሃለፊ ሪቻርድ ኮፐላን ማይልስ እና ወያኔን ያጠናከረች የየማነ ጃማይካ ውሽማ "የክርስቲ ክራፍት" ውጥን ጥረት በተግባር እየተተገበረ ነው።

ወያኔ እና ሻዕቢያ ሁለቱም ድርጅቶች የዓረቦችና የሲ.አይ.ኤ ንብረቶች መሆናቸው ለዓመታት የዘለቀው ግንኙነታቸው በግልጽ ይነበባል። የህ አሉባልታ ሳይሆን በጭብጥ በሴራው በአካል የተሳተፉ በስመምነቱ ላይ ቁጭ ብለው የዓይን ምስክረትነታቸው ለሕዝብ ይፋ ያደረጉት የአከለጉዛይ አውራጃ ዋና አስተዳዳሪ የነበሩት "አቶ ተስፋሚካል ጆርጅዮ" ምጽዋ



ላይ በደርግ ዘመን በምፅዋው ሲምፖዚዮም በዓል፤ ባቀረቡት እና እራሳቸው ባነበቡት ፅሑፍ በተለይ ኢሳያስ አፈወርቂ  የአሜሪካ የስለላ ድርጅት ተወካይ ሪቻርድ ኮፕላንድ ማይለስ



Richard Coplan Miles የተባለው ኢሰያስ ኣፈወርቂን በ1969 ዓ.ም.ፈ. ማለት ከ52 ዓመታት በፊት "ተከላ" ወይንም (ነርሰሪ)Seed Plantation Project" በመባል የሚታወቀው፤ ረቂቅ ብሮጀክት የተጠነሰሰብን ታላቅ ሴራ ላይ እንዲሳተፍ ቀጥሮት እንደነበረና፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሙሉ ትጥቅና ስንቅ፤መረጃና ማበረታቻ ይሰጠው አንደነበረ ድሮ የጀብሃ ታጋይ በኋላ ድርጅቱን ከድተው በሰላም ወደ አገራቸው በመመለስ በኢትዮጵያ ላይ ያነጣጠረ ጥቃት በማጋለጥ የታሪክ ባለውለታ የሆኑት ኤርትራዊው አቶ ተስፋሚካል ጆርጆ ገልጸውታል። ይህ መረጃ ይፋ በማድረጋቸውም በኢሳያስ እና በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ አገሬ ብለው ሰላምና መረጋጋት አለ ብለው ያለስጋት እኖራለሁ ብለው አዲስ አበባ ይኖሩ በነበሩበት ወቅት

ወያነ ትግራይ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ እቤታቸው ድረስ ስልክ ተደውሎ ትፈለጋለህ ተብለው ከቤታቸው ሲወጡ በነብሰ ገዳዮች ጥይት አዲስ አበባ ውስጥ ተገድለዋል።

ይህ “ተከላ”Seed Plantation Project" በመበል የታወቀው የሪቻረድ ኮፐላንድ ማይለስ ተልዕኮ አቶ ተስፈሚካል ጆርጆ ምፅዋ ላይ ያነበቡት የአማርኛ ሰነድ/ጽሑፍ አማርኛውን ተርጉመውና በሰፊው ተንትነው ያቀረቡት ወዳጄ እና መምህሬ አገር ወዳዱ አርበኛው የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር አለሜ እሸቴ ነብሳቸው ይማርና ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት በእኔው በድረገጽ (ኢትዮጵያን ሰማይ) እንዲለጠፍ የላኩልኝ እና ለድረገጾች እንዳሰራጨው የላኩልኝን ትርጉም “**MOTHER OF ALL CIA POLITICAL SURROGATES IN ETHIOPIA**

**How Richard / Miles COPELAND of the CIA recruited Isayas Afeworki in 1969**

**As told by Tesfamichael Giorgio**



**Aleme Eshete .”**

ማንበብ ጠቃሚ ነው። ከላይ ያለው ፎቶ ትልቁ ኢትየፐጵያዊ ው ሊቅ ፐሮፌሰር አለሜ

እሸቴ ናቸው። **Aleme Eshete The grandeur Scholar!!** የፕሮፌሰር አለሜ ጽሑፍ “ፍሮም ፋሺዝም ቱ ፋሺዝም” የሚለውን ሌላው የተደነቀው ምርምራቸውን ያንብቡ።ታሪኩን ለመጻፍ ካሜሪካ እኔ የላኩላቸውን የሪቻርድ ኮፕላን ማይልስ የጻፈው ፊክሽን መጽሐፍ (ለአፍሪካ ቀንድ ያለመው ፊክሽን የሚመሰል ሰነድ) ልኬላቸው በስፋት ካነነቡት በኋላ ነበር ጽሑፉን ያዘጋጁት።

ቀለተ አስፍሃ የተባለ ኤርትራዊ ጸሐፊ በትክክል እንዳስቀመጠው “የኤርትራ ሕዝብና ታጋይ ኤርትራን ለአሜሪካ መንግሥት እስትራተጂካዊ ጠቀሜታ እንዲሆን ነበር በሚያስብል መደምደሚያ ላይ በመድረስ መገመት የሚያስቸግር ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለው።” ይላል። በትግራይ በኩል ያሉት ምሁራን ግን ከኤርትራኖች ጋር አይጋሩም። ወያኔዎች የሚሉት ነፃነታቸው ያስገኘንላቸው እኛ ነን። ስለዚህም ላሜሪካኖችና ለዓረቦች ሳይሆን ኢሳያስ አምባገነን በመሆኑ አንጂ ሲ አይ ኤም ሆነ ዓረቦች እዚህ ላይ ተጠቃሚ አይደሉም፤ተቀጣሪያቸውም አይደለም ባይ ናቸው። ውሸት!

ወቅቱ የንጉሱ/ጉልተኛ ስርዓት ተቃዋሚ እየበዛበት በመሄዱ፤ አሜሪካኖችና እስራኤሎች ተራማጅ መሳይ ቡድን/ስርዓት ፍለጋ ላይ ነበሩ። እስራኤሎችም ስጋታቸው በቀይ ባሕር አካባቢ የተሰገሰጉት እስራኤልን የከበቡ ዓረቦች በተለይም “ብላክ ሰፕተምበር” (ጨለማው መስከረም) በመባል የሚታወቀው የፒ.ኤል. ኦ. ፓለስታይን የሽምቅ ተዋጊና ነብሰገዳይ በድን እስራሎችና አሜሪካኖችን ስላሰጋ፤ አምባሲያቸውና በተለይ ቃኘቀው ላይ ያለው ጣብያቸው በቦምብ እንዳይመታባቸው ስለሰጉ፤ “ጀብሃ” የሚባለው ኤርትራዊ የግንጠላው ጀማሪ ዓረባዊ

ባሕሪ የተላበሱ መሪዎቹ  ከፒ.ኤል.ኦ ያሲን ዓራፋት ጋር ግንኙነት ስለነበራቸው ስጋት ስላሳደሩ፤ በምትካቸው ተቀናቃኝ ሃይል ይፈልጉ ስለበር፤ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የሰላም ጉባኤ” በሚል የሰላም ንግግር ጥሪ እንዲጀመር ደብዳቤ ለተገንጣዮቹ በምስጢር ተልኮ ስለነበር፤ በወቅቱ የዘውዱ ስርዓት እና አሜሪካኖች ከፍተኛ የስለላና የምስጢር ግንኙነት የጠበቀ ስለነበረ፤ ምስጢሩ አሜሪካኖች እጅ መውደቁ ግድ ስለነበር፡ አሜሪካኖቹም ኢሳያስን ለማግኘት አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው፡፡ አሜሪካኖቹም እርቁን ለማሰናከልና ወደ ራሳቸው ጠቀሜታ ለማዋል አጋጣሚውን ተጠቅመው ወደ ራሳቸው የስለላ ጠቀሜታ ፕሮጀክት ጠለፉት፡፡ አጋጣሚ እና ክፍተት ሲገኝ ሁኔታዎችን በመጥለፍ ወደ ራሳቸው ጠቀሜታ አንዴት ይጠቀሙበት አንደነበር ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ደረግ እና እስከ ወያኔ ስርዓት ዘመን ቅጥረኞችን በማሰማራት አንዴት አንደሚጠልፉት በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

በዛወ ወቅት ሁኔታው ስላመቸላቸውም፤ በውቅቱ “የኤርትራ ጠ/ግዛት የሰላም ጉባኤ” ተብሎ በተሰየመው የሰላም ጥረት (ከኤርትራ ሽማግሌዎች/ሃይማኖት መሪዎች/ሰራተኞች ታላላቅ ሰዎች....ያካተተ ጉባኤ/ኮሚቴ) ለማድረግ በ1962 ዓ.ም ጥቅምት ወር ውስጥ ተቋቁሞ ነበር፡፡ የሰላም ጥሪ ጉባኤ መሪ የነበሩት

ደጃዝማች ገብረዮሐንስ ተስፋማርያም የተፈረመ የሰላም ጥሪ ደብዳቤ ተፈርሞ ከአስመራ ወደ በረሃ ለእነ ኢሳያስ ተላከ። እነ ኢሳያስ ይህንን ዕድል በመጠቀም “ሰላይ ድርጅቶቹም ከኋላ ሆነው ዕድሉን እንዲጠቀሙበት” ስለገፋፏቸው፤ የሚከተለው (ደብዳቤ ባጭሩ እጠቅሳለሁ) ጽፈው ከመንግሥት ጋር ግንኙነት ጀመሩ።

“ ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ መ/ጠ/ሐ/ሠ/ኤርትራ ከሜዳ” በማለት በ24/11/69 (እ.አ.አቆጣጠር) የተጻፈ ደብዳቤ “ከልጆቻችሁ ሓሳብ ለሓሳብ ለመለዋወጥ በፈለጋችሁበት ቀን ክቡርነትዎ በወሰኑት ቦታ በአክብሮት አንጠባበቃለን።”

በሚል አብርሃም ተወልደ እና ሰለሞን ወ/ማርያም በተባሉ ታጋዮች ተፈርሞ ወደ ኮሚቴው ወደ አስመራ መልስ ተላከ።በዚህ ወቅት ተስፋሚካል ጆርጆ (የአዲኧላ ወረዳ ገዢ) እና የኤርትራ ጠ/ግዛት ፖሊስ ም/አዛዥ የነበሩት ሌ/ ኮ/ል ገ/እግዚአብሔር መሐሪ እና አንድ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጀብሐዎቹን ለመገናኘት ወሰኑ። በተደረገው ጥረትም እነ ኢሳያስ “እኛ ከጀብሃ (ተ.ሓ፤ኤ/ጀብሓ) እስላሞቹ ጋር ተጣልተናል እኛ ክርስትያን ሃይሎች ነን እና ከእኛ ጋር ግንኙነት ማድረግ ከፈለጋችሁ ልጆቻችሁ ነን እና ንግገሩን እንቀጥል” ብለው በተስፋሚካል ጆርጆ መሪነት ግንኙነቱ ቀጥሎ እነ ሪቻርድ ኮፐላንድም እነ ኢሳያስን ወደ ቃኘው አስመራ አስመጥተው የስለላው መረብ ቅጥረኛነት በኤርትራ ምድር እንደ ጀመረ የታሪክ ሰነዶች ይመስክራሉ። ወያኔ የራሱን ቅጥረኛነት ገበና ለመደበቅ

ቢመጻደቅም የሁለቱ ቡድኖች ማንነት ሃቁ ይህ ነው፤፡ በሰፊው እመለስበታለሁ።

ፍስሃ ቀለታ የተባለ የኤርትራ ጸሃፊ፤ “ውጭ አገር ያለው እልፍ ፒ.ኤች.ዲ የያዘ ምሁር  በ ሲአይኤ የተመለመለ በቅጥረኛ የተሞላ ስብስብ በመሆኑ የኢሳያስ አፈወርቂ የሲአይኤ ፕሮጀክት/ተልዕኮ ላለማጋለጥ ሲሉ ኢሳያስ ሜዳውን እንዲቆጣጠረው ዕድል ሰጥታል። ያ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ የሆነው የኢሳያስ መንትያ ወንድም የሆነው የሲአይኤ ቅጥረኛው ወያኔ ትግራይም በበኩሉ (የጀብሃ ትላልቆቹ መሪዎች የስለላው መረብ ቅጥረኞች እና ተባበሪዎቻቸውን ወደ ጎን ትተን) የጀብሃን ድርጅት አጥፍቶ ለስለላው መረብ ዋናው ተጫዋችና ለስለላው አጋራቸው ለኢሳያስ አፈወርቂ ኤርትራን ለማስረከብ ትልቅ ሴራ ተጫወተዋል።” ይላል።

ጸሐፊው እንደሚለው፤ ዛሬም ከነፃነት በኋላ ይህ የስለላ ቡድን ገርስሶ እንዳያስወግደው የወያኔ ቡድን በትዕዛዙና በፍላጎቱ የሚንቀሳቀሱ ወያኔ ያደራጃቸው “ኪዳን” የተባለ ስብስብ ከውጭ አገር ወደ አዲስ አበባ በመጥራት የረባ ትግል እንዳይደረግ ሉዓሙን እየተቆጣጠረ ወደ በኋላ  እየጎተታቸው ኤርትራ ውስጥ የስርዐት ለውጥ እንዳይደረግ እንቅፋት ሆኗል። ለዚህም ነው ኤርትራ ውስጥ መንግሥትም ይሁን ተቃዋሚ የሚባል የለም የምንለው።” በማለት አዳዲስ የስለላ መረቦች በነባሮቹ እግር እየተተኩ እንደሆነ ጸሐፊው የኔን ሃሳብ የተጋራ ይመስላል።

ወደ ኢትዮጵያ ብንዞርም፤ ሴራው ያንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሴራውና ክንዋኔው ከኤርትራዊያኖቹ የባሰ ካልሆነ አይሻልም። ጥቃቶቹ በሁለት ወገን እንመለከታለን። ተቃዋሚ መስለው ለስለላ ድርጅቶችና ጸረ ኢትዮጵያ ሴራ ደፋ ቀና የሚሉት “በተቃዋሚ ውስጥ ያሉ ግለሰቦችና” “በቅጥረኛነቱ የማያፍር የወያኔ ትግራይ ድርጅት” በየበኩላቸው ያበረከቱት አገርን የመገዝገዝ ሴራ እንመለከታለን ።

መመልከት ያለብን ዓብዩ ስዕል ‘ሲአይኤም ሆነ የአውሮፓ ስለላ ድርጅቶችና መንግስታት ለወያኔ/ለሻዕቢያ እና እነሱን ለሚቃወሙ ተቃዋሚዎች ሁለቱን ወገኖች በጠየቁት መንገድ ታባበሪ ሆነው ለምን ይረዳሉ የሚለው ጠያያቂ መለስ ማግኘትና ለምን እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ስርዓት ተብለው ለሚጠሯቸው፤መሪዎችና ወኪሎቻቸው የሚንቀሳቀሱበት መድረክ፤ጥገኝነት፤ገንዘብ፤ጥበቅና፤ አገልግሎት (ፋሲሊተሽን) ይሰጣሉ። በሌላ ወገን ደግሞ ሁለቱንም የሚቃወሙትን ተቃዋሚዎች ለሁለቱ ስርዓቶች የለገሱትን አገልግሎት እና መድረክ እኩል ይለግሳሉ። ሴራው ግልጽ የሚሆነው እዚህ ላይ መሆኑን ልብ አድርጉ።

ይህ የሚሆነው ለምንድነው? ብሎ ለሚጠይቅ ጉዳዩን ጠለቅ ብለው ትንሽ ማብራራት ያስፈልጋል። አሁን ባለንበት እጅ አዙር (ፕሮክሲ አገዛዝ) ተራማጅ/ቀና/አገርወዳድ ኣፍሪቃውያን በማስወገድ ሥልጣን በሚስገበገቡ ቅጥረኞቻቸው በመተካት አፍሪቃን ያለ ጠመንጃ እንዲቆጣጠሩ እንዲያመቻቸው (ልክ እንደ ኢትዮጵያ ሁኔታ) ሁለቱንም ተቀናቃኞች( ስርዐቱና የስርዓቱ

ተቃዋሚዎችን)በማስጠጋት/መጠለያ/በመስጠት/መንከባከብ/መቀለብ/ማስተናገድ/ማስተማር/ስልጣና መስጠት የቀለለው እንደሆነ በነደፉት ተግባራዊነት አይተውታል።

ያገለገላቸው የስርዓት መሪ በሞት ድንገት ሲለይ ወይንም አገልግሎቱ አገባድዶ ፍቅራቸው አርጅቶ ወደ ቅራኔ እና ፍች ቢያዘነብል ተከታዩን ቅጥረኛ አገልጋያቸውን አዘጋጅተው መጠበቅ ስለሚኖርባቸው፤ "በፓርታይም" ቀጥረው ሲያንቀሳቅሱት የነበረውን ተቃዋሚ ቡድን ወይንም የውስጥ የስርዓቱ ድብቅ አገልጋያቸውን በምትኩ በመተካት ቁጥጥሩን ቀጣይ አንዲሆን ውስጥ ለውስጥ በመነጋጋር፤በረቀቀ ዘዴ ተቃዋሚውና ስርዓቱን ለሁለቱም አንደ አባትነት "እየተቈጡ/እየገሰፁ/እያግባቡ/ እያባባሉና አንዳንዴም ለማስመሰል እያወገዙ" አንዱ ባንዱ አገልጋይ ለመተካት ያመቻቸው ዘንድ ይህንን መንገድ ይወዱታል፤ ይከተሉታል። ምክንያቱም ሁለቱ ተጫዋቾች በነሱ ሜዳ ላይ እና በእነሱ ዳኝነት ስር ወድቃወልና፤በቀላሉ ፖለቲካው ይመዘምዙታል።

አምቢተኛነት እና አገር ወዳድነት ያሰዩ ጠንካራ አርበኞች ሲገጥማቸው ደግሞ በገዢው መደብ ሲታሰሩ "ይቅርታ ጠይቀው አንዲወጡና ለወደፊቱ ተቀናቃኝ ቢሆኑ ቀደም ብሎ በፍርደገምድል የተፈረደባቸው ዕድሜ ይፍታ ብይን አንደሚረጋባቸው" ሚና በመጫወት ሞራላቸው በመስበር ተከታዮቻቸው አንዲያወግዟቸውና አንዲነጠሉና ትግሉ አንዲዝል ሚና ይጫወታሉ።በወያኔና በሻዕቢያ ውስጥ የሲአይ ስራ አስፈጻሚ



ጃንዳይ ፍሬዘር፤ ('አደይ ኢታይ' የሰጠሿት ስም) በመሳሰሉ አዲስ አበባ በሚኖሩና አፍሪካ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ አምባሳደሮች በኩል የታዩ "ሴራዎችን" ስትመለከቱ የቅኝ አዙር አገዛዙን ሰንሰለት እንዳይበጠስባቸው ያደረጉት ዓይን አውጣ ሴራቸው ከሕሊናችሁ ትውስታው ደብዛው እንዳልጠፋ አርግጠኛ ነኝ።

ሰው ሳያስገድሉ፤ መፈንቅለ መንግስት ሳያደርጉ ፤ሕዝብ እንዲበጣበጥ ሳያደርጉ፤ ቀስቅሰናል ፤ወንጀል ፈጽመናል ብለው በጫና ይቅርታ ጠይቀው ከወያኔ እስር ቤት



Our Men and woman in Americaየወጡትንም አንዳንዶቹ የስለላው ድርጅት አገር ወደ ሆነው ወደ አሜሪካና አውሮጳ እንዲመጡ

በማድረግ ከትግሉ እና ከመታገሉ ከእንግልቱ ርቀው በመጪው ስርዓት ተተኪ እንዲሆኑላቸው የተቻላቸውን እንክብካቤ ያደረጉላቸዋል;። ላንዳንዶቹም ተራራ ላይ ወጥተው መጪው አገልግሎት እንዴት እንደሚከናወን በተሰጣቸው ‘ፖለቲካዊ ተከላ’ እንዲፈላሰፉና እረፍረት እንዲወስዱ ወጪው ሁሉ ይሸፍኑላቸዋል (ኢሳያስ አፈወርቂ ‘ከማይ ዓላ’ እስመራ ቃኘው ድረስ መጥቶ ያደረገው “የቬከሽን” ዕረፍት ማለት ነው)።

እንደሰለጠነው ሁሉ ኢሳያስ አፈወርቂም የራሱ ፕሮክሲ/የእጅ አዙር ተዋናዮቹን በማደራጀት ለመጪው ስርዓት የራሱ “ተከላ” በመትከል ያልተማሩትን ’በኢትዮጵያ ሰንደቃላማ ላይ ‘ሃውልት’ የለጠፈው ድምህት የተባለው የትግሬዎች ድርጅት ሲያሰማራ፤ ተማርን ብለው ራሳቸው የሚመጻደቁ ግብዞች ደግሞ ‘ግንቦት 7’ የተባለውን “ቅጥረኛ” ቡድን በግምባር ቀደም ላደራጀት እያባባለ፤ ገንዘብ፤ የመሸሺያ፤ መጠለያ እየለገሰ በሪቻርድ ኮፕላን ስልጠና የተማረውን ልምድ በአነግ ፤ በኦብነግ በሲዳማ ንቅናቄ እና በግንቦት 7 እና መሳሰሉት መጋዢዎች ላይ የሲአይኤ የልጅ ልጆች እንዲፈጠሩ አድረጓል።

ሰለዚህም ብደሩን ለመመለስ ሰልጣኞቹ የሪቻርድ ኮፕላን ተማሪው የሲአሳያስ ምስልና ስብዕና (ኢሜጅ) እንዲከቡ ሻዕቢያ ባዘጋጀው በየፌስቲቫል በመገኘት አሳፋሪ የምንለው የሻዕቢያ ስራ እየሰሩ ናቸው። (ይህ ፎቶ



ኤፍሬም ማዴቦ የተባለው ‘የግንቦት 7 የሕዝብ ግንኙነት ተጠሪ’ ሻዕቢያ ፈሲቲቫል አክላንድ ካሊፎርኒያ ድረስ በመጓዝ ከኤርትራዊት አንድ ወንድ ልጅ መውለዱን በማበሰር “ዘመዳችሁ ነኝ” አይነት መሳቢያ ከተጠቀመ በኋላ ኢትዮጵያዊያኖቸን እየዘለፈ ኤርትራኖችን ሲያሞግስና ሲቀባጥር የሚያሳይ ፎቶ ነው።)

ጥቂት ሰዎች የያዘ ጥምረት እያለ ራሱን የሚጠራ መሪ ነኝ የሚለን (በኢሳት ተሌቪዥን ላይ በከፍተኛ ሃላፊነት ተመድቦ ስራ ላይ ያለ) ‘አቶ ንአምን ዘለቀ’ የመሳሰሉት ግለሰቦችም ለሻዕቢያ ጥብቅና በመቆም “ዓለም በሞላ ያወገዘው” አልሸባብን በመርዳቱ “የይስሙላ” ማዕቀብ የተጣለበት ኢሳያስ አፈወርቂን በመደገፍ “መኸተ/ይካአሎ” ወዘተ እየተባሉ ከሚጠሩት የትግራይን ሕዝብ “አጋሜ” አማራውን “አድጊ” እያሉ የሚዘልፉ የሻዕቢያ ደጋፊ ወጣቶች ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ሰንደቃላማ እያወለበለበ ከመሰሎቹ ጋር ሆኖ “ማዕቀቡን” በማውገዝ ሰላማዊ ሰልፍ ከወጡት ሻዕቢያ አገልጋዮች ጋር አብሮ መቀላቀሉን በስዕለ ደምፅ ተቀርጿል። ከሚገርመው ደግሞ “ኢትዮጵያ የምትባል አገር እስከ 4ኛ ክፍል በላይ እንዳንማር የከለከለቺን ኮሎኒያሊሰት አገር የማዕቀቡ ግምባር ቀደም ሴረኛ ኢትዮጵያ ነች” እያሉ TV ቃለ

መጠይቅ ላይ ከሚዋሹ የሻዕቢያ ወጣቶች ጋር ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጉ እጅግ ያሳዝናል። የሻዕቢያው መሪ አማርኛ መናገር የሚጸየፍ ዘረኛ ፍጡር ከመሆኑ አልፎ አማራን እስከመግደል ያደረገው ወንጀል ሳላስታውስ አላልፍም። "*EPLF* In one such incident, Issayas stopped a public bus, separated all the Amharas and Tigreans from the rest of the passengers, and shot and killed all of the Amharas and Tigreans. (Getachew Gebre, "Honeymoon Over," New African, December 1991, p. 19)"

የጥቃቱ ተዋናዮች እንደየፈርጁ የተለያዩ ናቸው። ሁላችሁ የምታውቁት 'አፍቃሬ አነግ" ጸረ አማራውና ጸረ ሚኒሊክ የሆነው ኤርትራዊው የሻዕቢያው ሰላይ ተስፋዬ ገብረአብም የተቻለውን ያህል የጎሳ ጽዳት በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ በሚጥርበት ባሁኑ ሰዓት ልዩ ቦታ እና ክብር ተሰጥቶት በግንቦት7፤ኢካዴፍ ኢትዮጵያን ካረንት አፊይርስ በተባለው ድረገጽና ፓል ቶክ፤ ኢትዮጵያን ሪቪው፤ እንዲሁም ኢሳትና ዘሐበሻ እንዲሁም በክንፉ አሰፋ የሚዘጋጀው ኢ ኤፍ ኤም በተባሉት ድረገጾች ስራዎቹን እንዲያስፋፋ ወይንም ወይንም ሰውየው እንዲገን እና ቀና ኢትዮጵያዊ ነው ለማሰኘት 'የፖለቲካ ተንታኝ አድርገው በማቅረብ የሕሊና አጠባ ዘመቻው እንዲያደርግ አስተዋጽኦ እያደረጉለት ይገኛሉ። በተጨማሪም የኢትዮጵያን ሪቪው ድረገጽ አዘጋጅም

ኤልያስ ክፍ  ሌ በኢሳያስ አፈወርቂ ላይ ያለው እምነት እና ስለ ሰውየው ስብእና የጻፋቸው ጽሑፎች እና የመሳሰሉ መሰል ተዋናዮች የሚሳተፉበት አፍራሽ እንቅስቃሴ ስንመለከት የግዝገዛው ሴራ በጥንቃቄ አንድንከታተላቸው ጠቋሚ አዳዲስ የአደጋው አማላከች ምልክቶች ናቸው። ከላይ የሚታየው የመጀመሪያ ፎቶ በቅርቡ አሜሪካ አገር ውስጥ 'የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅተቶች "የሽግግር መንግሥት" ተብሎ የተመሰረተው ከፍተኛው የአመራር አባል አቶ ስለሺ ጥላሁን ነው። መሃል ላይ ያለው አስመራ ውስጥ የተነሱት ፎቶ ኢሳያስ አብሯቸው ያለው ነው። ወደ ቀኝ መጨረሻ አለው አቶ ኤልያስ ክፍሌ ነው።

እንደዚህ የመሳሰሉ "ፖለቲካውን እንቀይራለን" በሚል አዛናጊ አዳዲስ ባሕሪዎች በጠላት ካምፕ ተገኝቶ ከጠላት ጋር ጠበል መራጨቱ የቅጥረኛነት ፈር ቀዳጆቹ ህ.ግ.ሓ.ኤ. (ሻዕቢያ) እና ህ.ወ.ሓ.ት ባሕሪ ወደ ኋላ ቆም ብለን አንድንመለከት ያስገድደናል። እንዲህ ያሉ ነጸብራቆች ከሰማይ ዱብ ብለው የሚከሰቱ ሳይሆኑ በአጥቂዎች በኩል በጥንቃቄ የተነደፉ ሲሆኑ፤ ሰለባዎቹ (አንዳንዴም የወስጥ አርበቻቸው ሊሆኑ ይችላሉ) ከአጥቂዎቹ ጋር ሊኖራቸው የሚገባ ግንኙነቶች በሚያቀርቡት አገልግሎትና በሚሄዱት ርቀት ይመዘናል።

## The Rape of Ethiopia by the Zionists Jews!!

አጼ ቴዎድሮስ ዛሬ ቢኖሩ የራሳቸው ትውልድ ቦታ የቆራ ማሕበረሰብ ወደ “ፈረንጅ/ነጭ አገር እየተጓዘ፤ ነጭ የወለደህ የነጭ ዘር ነህ” ተብሎ “የሁለት ሺሕ አመት ተረታ-ተረት” ልበወለድ (ፊክትሽስ) መሰረት አደርጎ፤ በሃይማኖት ሰበብ፤ ወደ እስራል ወደ ነጮቹ አገር ሲወሰድ ቢያዩና ቢሰሙ ምን ይሉ ነበር?

የትውልድ 

መንደራቸው የሆነው “ቆራ” በተባለው ገጠር ጎንደርና በመሳሰሉ አካባቢዎች የነበሩ ኢትዮጵያዊያን የአይሁድ/የፈላሻ ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያዊያኖች “እስራኤሎች፡ ናችሁ ብለው” በረሃብ እና በድህነት በበሽታ ኑሮ ውስጥ አንደማንኛችንም የሰቃዩ በመኖራቸው፤ ድህነታቸውና ያለ መማርነታቸውን ክፍተት ተጠቅመው በቀላሉ በማሞኘት “የፖለቲካ እና የሃይሞኖት የስነ ኣእምሮ አጣባ” ተፈጽሞባቸው በሺዎቹ ዘመኖች የነበረው ፈታሪክ

ተመርኩዘው በው  ስጥ አርበኞች አጠባ በሰፊው ለዘመናት ከተሄደባቸው በኋላ፤ እናንተ ጥቁሮች አይደላችሁም “ፈረንጆች እስራል አያቶቻችሁ” ንግሥተ ሳባን ወደ አገሯ ወደ ኢትዮጵያ ስትመለስ አጅባችሁ ወደ ኢትዮጵያ የመጣችሁ “ከ2000” ዓመት በፊት እስራል ዜጎች የነበራችሁ

ፈረንጆች ናችሁ እና ኢትዮጵያን ለቅቃችሁ ወደ እስራል ወደ አገራችሁ እንውሰዳችሁ በማለት በዘመናዊ ባርነት በገንዘብ ገዝተው ለማሸጋገር በስለላ የተቀጠሩ ቅጥረኞቻቸው፡ ለምሳሌ

አንደ እነዚህ የመሳሰሉት ግለሰቦች 

ቆራን ለቅቆ ወደ እስራኤል ከሄደ ከ40 አመት በኋላ በአይሁዶቹ ተቀጥሮ ተመልሶ የሴራቸው ተባባሪ በመሆን ወደ ገጠሪቱ ቆራ በመሄድ እኛ አስራኤሎች እንጂ "ኢትዮጵያ አገራችሁም የትውልዳችሁ መሬትም አይደለችም" በማለት በየበረሃው አቋርጠው አገር ከሚገዙ ቅጥረኞችና ስርዓቶች ጋር በመነጋገርና የስለላ መረባቸውን በመዘርጋት በድብቅና በግልጽ ሕዝቡን በማሸሽ (ኦፐረሺን ሰለሞን፤

 ኦፐረሺን 

ሙሴ......ወዘተ....ወዘተ..... በሚል የጥቃት ዘመቻ) በጥቁር ሕዝብ ላይ በኢትዮጵያ ሉአላዊ ሕዝብ ማንነት የተከናወነው አገርና ሕዘብን በማፍረስ የተፈጸመው ድፍረትና ወንጀል ተባበሪ ቀንደኛው የሴራው አስተባባሪና አስፈጻሚ ግለሰብ ከላይ የምታዩት

ፎቶግራፍ አንደኛው ይህ ግለሰብ ነው። አጼ ቴዎድሮስ ዛሬ ቢኖሩ ምን ይሉ ነበር?

ሕዝባችን ትውልዳቸው፤ደማቸውና ማንነታቸው ፍቀው "በሃይማኖት ሽፋን" ሌላ ማንነትን በማከናነብ የዚህ ስለላ መዋቅር



(የሲ አይ እና የሞሳድ) መርሃ ግብር በኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት የተቃጣ ጥቃት የተከናወነው ሴራ በጣም አሳዛኝና አንጀት የሚያሳርር ውርደት በውስጥ ቅጥረኛ ባንዳዎች ተፈጽሞብናል። ይህ ህፃን ማንነቱ ተነጥቆ ነጭ ነህ ተብሎ የተወሰደ ነው። ባንዳንድ ተንታኞች "ኦፐረሺን ሶሎሞን"



የተባለው "ኦፐረሺን ሰሌቨሪ" በማለት የሚጠሩት ሕዝብን (ህፃናትን) የሚዘዝርና የማፍለስ ዘመቻ 'የስለላ መረቦቻቸው' በሕዝባችን ላይ ያደረሱት ጥቃት እና ጉድ በዓይናችሁ ለመመልከት ይህንን ቪድዮ ተመለከቱ፡- ተከታይ Operation "Solomon" May 24th-25th, 1991 http://youtu.be/lENG40DSOpI ይህ በፊልም ሰነድ ተደግፎ የቀረበው የተመለከታችሁት ውርደትና ጥቃት በውስጥና በውጭ የስለላ ተባባሪዎቻው የደረሰብን የጥቃቱ አሳዛኝ ዘመቻ ነው። ይህ ሰነድ ስትመለከቱ ምን ተሰማችሁ? እራሳችሁን አስኪ ጠይቁ! ማን ነው ለዚህ ውርደት የዳረገን?

የራሳችን ሰዎች!~ ሌላ ቀርቶ አዛውንት የአገር መሪ ቀሳውስት በ80 ዓመታቸው፤አልጋ ላይ የበሽታ ቁራኛ የሆኑ እናቶች በሽተኛ ሽማግሌዎች  ሳይቀሩ ማንነታቸውን በረቀቀ ዘዴ በማስካድ በምስጢር እና በይፋ የአእምሮ አጣባ ዘመቻው በላያቸው ላይ ከተጠናቀቃ በበኋላ፤ “የካቴና ሰንሰለት በአእምሮአቸው ጠልቆላቸው”፤በሰማይ በአይሮፕላን፤ በእግር በየምድረባው በሱዳን በረሃ በጣረሞት እየወደቁ እየተነሱ በሰንት ስቃይ ሕዝቡን እየመሩ ቄሶች ወደ ፈረንጆቹ አገር ወደ እስራል እንዲፈልሱ ተደርጓል።



የተከታይ ቅጥረኛ የስራ አፈጻጸም ፋይል ስትመለከቱ ያሳዝናል። ዚዮናዊያን አይሁዶች በሕዝባችን ላይ እና ባገራችን ድፍረት ያደረሱት በደል በተቀነባበረ እና ልብ በሚሰብር ጥቃት በስዕለ ድምፅ ያለ ምንም ስጋትና ተጠያቂነት አገራቸውን እና ገጠራቸውን ለቀው የሄዱት ፈላሻዎቹ “መሬታቸው ጭር ብሎ” ባዶ እንደ ቀረ ‘የጠለፋው ተርዒት’ ለዓለም ሲያሳዩ ንቀታቸው መጠን የለውም። ለምን ፈላሻ ትለናለህ የሚሉ አይታጡም ይሆናል (ብዙ አጣባ ስለተደረገባቸው አልይዝላቸውም)። አይሁዶች ብዬ የምጠራቸው ምክንያት ፈላሻዎቹ ኢትዮጵያዊያን አንጂ፤ አይሁዶች ስላልሆኑ ነው። አይሁድ ማለት እስራል ውስጥ የተወለደ አይሁዳዊ

ፈረንጅ ማለት ነው። ፈላሻ የተባሉበት ምክንያትም ኢትዮጵያዊያን ሆነው "የአይሁዶች ሃይማኖት ስለሚከተሉ" አይሁዶች ከሚባሉት ፈረንጆች ለመለየት ነው። ልክ ኢትዮጵያዊያን እስላሞች፤ 'እስላሞች' እንጂ 'የኢትዮጵያ ዓረቦች' እንደማይባሉ ሁሉ፤ ፈላሻዎቹም 'የኢትዮጵያ አይሁዶች' ማለት አግባብነት የለውም። ይልቁንስ እዛው ከሄዱ በኋላ "ፈረንጅ አይሁዶቹ" ፈላሻዎቹን 'ኩሺ" (ባርያ/ኔገር) እያሉ ሲሰድቧቸው መስማቱ እጅግ ያሳዝናል። "ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ" ነው የሚባለው?

ከላይ "ተከታይ" የሚል በፎቶግራፍ የተለጠፈው የጥቃቱ ዘመቻ 'ሰነድ' የሚነበበው 'የኢትዮጵያዊያን ታሪክ ይቀጥላል' ይላል። ኢትዮጵያዊያኖቹ አይሁዶች እንጂ ኢትዮጵያዊያን አይደሉም እያሉ በሌላ ወገን ደግሞ፤ የኢትዮጵያዊያን ታረክ ይቀጥላል ይሉናል። ነገሩ ባገሪቱ ላይ የተሰነዘረው ጥቃት አያቆምም እያሉን ነው። የሚቀጥሉት "ኢት ጵያዊያንስ" እነማን ይሆኑ? ቅጥረኛ እና ተከታይ እስካለ ድረስ ጥቃቱ ቀጣይ ነው። ጥያቄው ግን 'ቀጣዩ ጥቃትስ የት እና በማን ሃይማኖት ላይ ይሆን?" ነው።

ደርግ ሊወድቅ ሲል ወያኔ ሊገባ ሲል እስራሎች የተጠቀሙበት ሀረግ ልጥቀስላችሁ May 24/1991 "Operation Solomon is underway to bring the remaining Jew bring home. The mission has to accomplish in very short time. The plane is on its final landing approach. Below, it is the capital city of Ethiopia –Addis Ababa, a city threatened and surrounded by rebel forces and control by government

forces on a verge of total collapse. One thing is clear. There is a *unique* window of opportunity to bring now the 15,000 thousand remainder Ethiopian Jews home who were living surrounding the Israel Embassy building in Addis Ababa. The legend has promised them, that 'rescue and redemption will come from heaven and will be carried and they will be carried on eagle's wings to Jerusalem'. Now, finally the dream has come true!" *(ዩኒክ ዊንደው ኦፍ ኦፖርቱኒቲ"* የምትለዋን ሐረግ እና *"ረስክዩ"*



የምትለዋ ቃላት በደምብ መርምሯት። ኢትዮጵያ ጠባቂ ባጣችበት መዝግያዎቿ ተሰብረው ክፍት በሆኑበት ወቅት ነበር "ፈረንጆቹ" ይህንን ዕድል ተጠቅመው ያለ ምንም ቁጥጥር ሉአላዊን ያገራችን መሬትና ሰማይ ተጋፍተው 'ሕዝባችንን ሰልበው በተረት ተረት የህሊና አጠባ ተጠቅመው ነው የወሰዱዋቸው"። ከላይ የሚታዩት ሁለት ሰዎች፤ አሜሪካው እና እስራላዊው አምባሳደሮች አዲስ አበባ አየር ማረፊያ ላይ የማጓጓዙ ሂደት ያለ ምንም "ማን ነህ?" ባይ፤ የፈለጉትን ሕዝብ እየጋፉ ወደ አይሮፕላን ውስጥ ሲወስዱ የበላይ ተቆጣጣሪ በመሆን የውስጥ አርበኞቻቸውን የስራ ውጤት በደስታና ትርኢቱን ሲከታተሉ ነው። መሪዎቿ ከድተዋት ተከላካይ አጥታ ዚአኒስቶቹ ጉያዋን ሲደፍሩ የታየ ክንዋኔ የሁላችንን ስንፍና የሚፈትሽ የጥቃት ክንዋኔ ነው።

ቀጠል ያደርግና ሰነዱ የሚለው፡- “በረዢም ድርድር ሲጓተት የነበረው የኢትዮጵያ አይሁዶች ወደ እስራል የመውሰድ ክንዋኔ የተጠናቀቀው በአ 

ሜሪካኖች ጣልቃ ገብነትና ተደራዳሪነት እንጂ አሜሪካኖች ባይደራደሩልን ኖሮ ሁኔታው እንደምንጠብቀው አይሳካልንም ነበር”[redacted] (the protracted negotiat 
ions with Ethiopian government could not have reach an agreement without the help of the Americans.” ይላል ናይም 

/Naim/ የወቅቱ (1991) አምባሳደር በኢትዮጵያ።

ኑብስ ይማር ኢትዮጵያዊው የታሪክና የፖለቲካ ሊቅ ክቡር አለሜ እሸቴ ካልሆኑ በስተቀር ሌሎቹ የታሪክ ምሁራኖቻችን ይህ ዘመናዊ ባርያ የማስተላለፍ ገበያና ስራልኝ ልስራልህ ‘የልውውጥ ሴራ’ እና

በማንነታችን ጥቃት ሲፈጸምብን ለስሙ የተሸከሙት ዲግሪያቸው ሳይጠቀሙበት ትንፍሽ አለማለታቸው አስገራሚ ክስተት ሆነብኛል።

ይህን አሳዛኝ የባንዳዎች ሴራ እና ተሳትፎ ስትመለከቱ የውስጥ ተባባሪዎቻቸውም ሆኑ ዓረቦች ነገ እስላሙን ዓረባዊው መሓመድ ቤተሰቡን ወደ አበሻ ምድር ሲልክ አብራችሁ ወደ አበሻ ምድር የተጋዛችሁ "የኢትዮጵያ ዐረቦች" ናችሁ እና ወደ መዲና አገራችሁ ወደ ሳወዲ ተመለሱ ብለው በወኪሎቻቸው የአእምሮ አጠባ ዘመቻ አይጀምርም ማለት አንችልም (ለነገሩ የ አጋዴን ነፃ አውጪው ሊቀ መንብሩ "አጋዴኖች/ሶማሌዎች ዓረቦች ነን" ሲል የሰጠው ቃለ መጠይቅ ካሁን በፊት አቅርቤላችሁ ነበርና ይህም የተንጠለጠለብን ጉድ መኖሩን አስታውሱ) ። ነገ የኦሮሞ ሕዝብ አንዲህ ናችሁ፤እስራኤሎች ናችሁ፤የአብርሃም ልጆች ናችሁ ፤ መጽሐፍ ቅዱስ፤ዘፍጥረት ውስጥ ስማችሁ ፤ ነገዳችሁ ተጠቅሷል ወዘተ....ወዘተ... እያሉ ኢትዮጵያዊያን አይደላችሁም እና ተጋዙ ብለው ቅጥረኞች አዘጋጅተው ዘመቻው አያጧጡፈትም አይባልም። እንደያው ለነገሩ፤ በቅጥረኞቻቸው በኩል አሮሞቹን-አበሾች አይደላችሁም፤ ኢትዮጵያ አይደላችሁም... እያሉ የግንጣላውና የማፍረሱ ሴራ ቅጥረኛነታቸው በሰለላው ድርጅት እየታገዙ ከጀመሩት ከ40 አመት በላይ ሆናቸዋልና "አያም በሉ" አለ ትግሬ (የሆድ በሆድ ይዛችሁ-ረጋ ብላችሁ ሁሉንም አስተውሉ ማለት ነው)። ሊሆን ይችላል! ቅጥረኛ ሲበዛ ለምን አይሆንም? ነገ የሞሳዶች ወይንም የዓረቦች አይሮፕላን በድብቅ ወይንም በግሃድ አሮሞ መሬት፤ወሎ መሬት፤ሐረር መሬት፤አደሬ መሬት ላይ

ሊያርፍ ይችል ያሁናል። አይሆንም ብሎ በእርግጠኝት የሚከራከር ሞኝ ብቻ ነው።አይሆንም ያልነውን ሲሆን ካየን ከንግዲህ ወዲያ እንዴት አፍ ሞልቶ መከራከር ይቻላል?

ከማገባደዴ በፊት በዚህ ላጠቃልል። መጀመሪያ የማንነት ቡርቦራ በማንም ጎሳ ላይ ከተካሄደ ቀጣዩ የማፍረስ ሂደት ማከናወኑ ቀላል ነው። እንደትመለከቱት ከላይ ያመላከትኳችሁ ቪድዮው ሲፈጸም 'የምታዳምጡት መልእክት' "የመጨረሻው ፈላሻ ህጻን ከኢትዮጵያ 'ሺፕ' ተደርጎ/ተጠርጐ እስኪ ወጣ ድረስ የማጋጋዙ ስራ እገሌ እና እገሌም አብረው እዛው አፔረሺኑ ውስጥ መሳተፋቸው ይቀጥላሉ" ትላለች አዘጋጅ ጋዜጠኛዋ አይሁዳዊት። የመጨረሻው ህጻን የተባለውም ይከላይ አስቀድሜ በፎቶግራፍ ሰነድ የተደገፈው የጥቃት ታሪክ ባለፈው ወር ተጠናቋል። ጽዮናዊያን እስራለሎችና ወያኔዎች እንዲሁም የደርግ መሪውና በዛው ድርጅት የተዋቀሩ የጥቃቱ ዘመቻ ተዋናይ ሰላየች "ምን ታመጡ!" ብለው ህዝባችንን ከምድራቸው አስወግደው በገንዘብ ተሸጠው ወደ እስራል አግዘዋቸዋል። ያ አልበቃ ብሏቸው ጥቁር ሕዝብ በምድራቸው እንዳይራባ መርፌ ወግተው አስገቧቸው። የባንዳዎች ሴራና ጥቃት እስካላጋለጥን ድረስ ሴራው አሁንም ለወደፊቱም ይቀጥላል። የሰው ልጅ በሃይማኖቱ ምክንያት ማንነቱና አገሩን ጥሎ የሌላ ባዕድ ሰው ነኝ እንዲል ያለ ምንም ምጉትና /ራሺናል/ወጣሪ ክርክር በየመጽሐፍቱ ተረታ ተረቶች እየተከተሉ ለዘመናዊ እምሮ አጣቢዎች አመቺ መንገድ ሆኖላቸዋል። አስደንጋጭና ወደር የሌለው ጥቃት "በፅዮናዊ አይሁዶች" ያለ ጠመንጃ በኢትዮጵያ ምድር ሲፈጸም ይህ የመጀመሪያውና ተወዳዳሪ የሌለው ዘረፋና

ጥቃት ነው! እውነትም ወንጀሉና ጥቃቱ "ዘ ሬፐ ኦፍ ኢትዮጵያ ባይ ዘ ጂውስ!" ብየ መሰየሜ ተገቢ የወንጀሉና የጥቱ መገለጫ ነው።

ወደዚሁ ወደ ዛሬዎቹ አዳዲስ ባንዳዎች ልመለስና ልደምድም።

ወደ ግንቦት7!!

የግንቦት 7ቱ ዋና ጸሐፊ አንዳርጋቸው ጽጌ በኢሳት ቲ/ቪ ላይ ቀርቦ ለሕሊና በሚሰቀጥጥ፤ብዙ ኢትዮጵያዊ ያደመጠው የሰጠው ቃለ መጠይቅ በሌሎቹ አጋር ወዳጆች ብዙ ስለተጻፈ ትንሽ ልበልና ልደምድም። የኤርትራን ሕዝብ በውሸት እያታለለ፤በጥይት እየረሸነ፤በገራፊዎች እያስገረፈ፤ወጣቶች ከእናቶቻቸው ጉያ እና ከትምህርት እየነጠቀ፤ወጣት ወንዶችና ወጣት ልጃገረዶች ወደ በረሃ በማጓጓዝ በወታደራዊ ስልጣና ስም ለመኮንኖቹ ልብስ አጣቢና ተኳሽ፤ ምግብ አዘጋጅ እና የጭን ገረድ በማድረግ 30 ዓመት በሳሕል፡ ለ22 ዓመታት ደግሞ አስመራ ላይ ሆኖ ብጠቅላላ ለ52 ዓመት ኤርትራኖችና ኢትዮጵያኖችን ጭምር ደም ያፈሰሰው ወንጀለኛውን ኢሳያስ አፈወርቂን ሲያሞካሹ፡ ማድመጥ የ100 አመቱ ኢትዮጵያን የማፈራሱ የኮፐላን ማይለስ የስራ ቤት "ተክል" ስራ ላይ ቀጣይነትን ያሳያል።

ኢሳያስን እዚህ ድረስ ያደረሱት ሲአይኤ፤ሞሳዶችና ዓረቦች እንደሆኑ እናውቃለን። በነዚህ የስለላ ድርጅት እና አንክብካቤ ያደገ ግለሰብ በግንቦት 7 መሪዎች ሲሞገስ ማድመጥ አገልግሎታቸው ምን ያህል ርቀት አንደሄደ ግልጽ ነው። ዐረቦች

እና የመሳሰሉት በባለቤትነት ቢጋሩትም ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ሻዕብያ እና ወያኔ የሲአይኤና የሞሳድ ንብረቶች/መገልገያዎች አንደሆኑ ብዙዎቹ ይስማሙበታል። የአሜሪካ እና የእስራል ስለላ ተጠቃሚና ተቀጣሪ የሆነው ኢሰያስ ኣፈወርቂ ከ1969 ዓ.ም.ፈ. ማለት ከ52 ዓመታት በፊት የተተከለ የስለላው መረቡ "የተከላ" Seed Plantation Project" የሚያነጣጥረው በኤርትራኖች ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንም በቀጣይነት ለማደፍረስ የተወጠነ ውጥን ፕሮጀክት/ውጥን ስለሆነ ግንቦት7ም ሆነ መሳይ ተገንጣያች ኤርትራ ውስጥ እንዲሰለጥኑ ሲፈቀድላቸው ያለ ምንም "አንካ አምጣ" (ጊቭ ኤንድ ቴክ) ፖሊሲ አይደረግም (ብርሃኑ ነጋም ግማሽ ሚሊዮን ብር ሲለገስለት ፤ ለጓሹ አገር "ምስጋና አንፈልግም፤ ለኛ እርባና ስንል ነው እየሰጠኛችሁ ያለው፤ አለን"። ብሎ ሳይደብቅ ነግሮናል፡ በምስጢር ሾልኮ በወጣው የምስጢር የድምፅ ቅጅ። አስፈሪው ሁኔታ እንዲህ እያለ የሻዕቢያው ኢሳያስም ሆነ የወያኔው መለስ ዜናዊ የተከተሉት ሴራ የግንቦት 7 ሰዎችም በብዙ መልኩ እየተከተሉት እንደሆነ ተግባራቸውና ንግግራቸው ያስታውቃል።

በመጨረሻ ሪቻርድ ኮፐላንድ በኤርትራ የተከለው 'ተክል' እንዲያብብ ኮፐላንድን የተኩት የዛሬ ፖሊሲ እና ሴራ ቀያሾስ እነማን መሆናቸው በስእላዊ መግለጫውንና አንዳንድ ሰነዳዊ መረጃዎችን ተመልክተን እንደምድም፡፡

ደርግ እንዲወገድ ኢሳያስና መለስ እንዲተኩ ያቀነባበሩት ሰዎች እንማን ነበሩ?

በሻዕቢያና በወያኔ እጅ አዙር ጦር (ፕሮክሲ ዎር) ተጠቅመን ደርግን በማስወገድ፤ መንግስቱን ወደ ዝመባብዌ በሰላም እንዲኖር ምስጢራዊ ድርድር በማድረግ ክፍተት በመፍጠር ወያኔን አዲስ አበባ፤ ሻዕብያን ኤርትራ ላይ አስቀምጠን የሶቭየተን ሃይል ከቀጠናው ማስወገድ በሚል እቅድ በማውጣት ኢትዮጵያን ያለ ወደብ ማስቀረትና ማዳከም የሚለው መርሃ ግብር እንዲተገበር መሪ ያደረጉት በረሃ ውስጥ ከሻዕቢያ ሽምጥ ተዋጊ አብሮ ለብዙ አመታት የኖረ በጋዜጠኛነት ሽፋን ኢትዮጵያን ሲሰልል ቆይቶ ወደ ኤርትራ በረሃ በጋዜጠኛነት ስም የተሻገረው አሜሪካዊው የስለላው መዋቅር አጠናካሪውና አደገኛው ሰላይ ጸረ




ኢትዮጵያ Dan Conell ያሁኑ

ፎቶግራፉ ደግሞ እነሆ  ከሱ በፊት ሪቻረድ ኮፐላንድ ትቶለት የሄደው አፍራሽ የተከላው ተልእኮ ከኢሳያስ ጋር አብሮ ኤርትራ በረሃ ላይ በመኖር የተሰጠው አፍራሽ የቤት ስራ ሲያከናውን ከተማ ውስጥ ደግሞ አይሁድ-አሜሪካዊው "ሄርማን





ኮኸን እና አፍራሽ ተልዕኮ ተባባሪ ልጆቹ"  ጋር ሆኖ ኢትዮጵያን የማፍረሱ ክንዋኔ ዋና መሃንዲስ በመሆን ከእነ ቡሽ እና





ደላላው ጂሚ ካርተር ከቅጥረኞቹ ከወያኔ እና ከሻዕቢያ ጋር (ሱዳን

ካርቱም ውስጥ) እየተገናኙ አደገኛ ጸረ ኢትዮጵያ ዘመቻቸው አከናውነዋል።



## ጆርጅ ቡሽ እና የሲ.አይ.ኤ ልጆቹ ግራና ቀኝ።

አባት ለልጅ ያስተላለፈለትን የሲአይኤ ተልዕኮ በኢትዮጵያ እንዲጠናከርና የውስጥ ተባባሪዎቻቸው እንደ መለስ ዜናዊ የመሳሰሉት ለቀጣሪዎቻቸው



መዳሊያ ሲሸልሙ ታይተዋል። ወደ ኤርትራ በመጓዝም ሌላኛው ትልቁ የሲአይኤ ልጃቸውን ያፈራው ውጤት ለመጎብኘት

 ሚስስ ክሊንተን (ወ/ሮ መድህን) ወደ አስመራ ተጉዛ በዓረብና በሲአይኤ አጋዥነት የተተከለው ሕገ ወጥ የሻዕቢያ ባንዴራ ጎን በመቆም የሲአይኤ ውጤት መሆኑን ለማሳየት ባበሻ ልብሳችን አጊጣ ተኩራርታብናለች።ባልዋ ደግሞ    ሁለቱ የሲአይኤ ፍሬዎች 'የአፍሪካ ተስፋዎች" በማለት በውስጥ ተዋቂ አነጋገር ነግሮናል። ይህ ከነገረን ጥቂት ጊዜ በኋላ ተሰምቶ ታይቶ ማይታወቅ የኤርትራ ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብ በመድፍና በመትረየስ በቦምብና ባይሮፕላን ተፋጀ። ደም እንደጎርፍ ፈሰሰ፤ ህጻናት በክላስተር መረዝ ባይሮፕላን ቦምብ ተደበደቡ።ሴራ አንድ እና ሁለት ተጠናቀቀ። አንድ ግንጠላ፤ ሁለት እንደገና ጦርነት! ሴራ አንድና ሴራ ሁለት ያለ ምንም ተጠያቂነት ተገባደደ።ገደይም የጦርነት ቆስቋሽም፤ ተባባሪም፤ደምበር ክፍት አድርጎ ለጥቃት

ያጋለጠም ምንም ሳይከሰሱ፤ ምነም ሳይሆኑ "ሁሉም እስከዛሬ ድረስ በስልጣናቸው ላይ አሉ"።የተወነጀለ፤ የተከሰሰ የለም። የሞተ፤ሞተ!!! ዝም! ዝም ሆነ።

ይባስ ተብሎ ዛሬም ኢትየጵያዊያን ኤርትራ ድረስ እየተጓዙ የኤርትራ ወንበዴዎች ሕዝባችን በመግደላቸው ሙገሳና ማሞካሸት አንደቤት ስራ የያዙት እንደ እነ አንዳርጋቸው ጽጌ የግንቦት 7 ነባር ባንዳ



ሰሞኑን ብቅ ብሎ ያጠቡትን ሕሊና ሲጨምቅብን መስማት ደግሞ ሌላው አስገራሚው የሰሞኑ ክስተት ሆኖብናል።

ኢሳየስና መለስ እጅግ ሲበዛ ምስጦች ስለነበሩ ስልጣን ለመያዝ የስለላው ስራ አዋቃሪዎች ካርቱም ድረስ ሄደው በእንዲህ ነበር የተጠናቀቀው። ከዚህ በታች በቅንፍ የተገኘው ሰነድ መመህር ቀለተ አስፍሃ የተባለ ኤርትራዊ ካቀረበው ጽሑፍ ነው። ከዚህ በፊትም እኔ ከተለያዩ ሰነዶች ያጠናከርኩት በድረገጼ ላይ ኢሳያስ አፈወርቂ ባሜሪካን ስለላ አማካይነት በሱዳን መፈንቅለ መንግስት

እንዴት እንዲከናወን ተልእኮ እንደተሰጠው ከዘረዘርኳቸው ሰነዶች የሚመሳሰል ስለሆነ የአስፍሃ ቀለተን አጭር ሰነድ አቀርብላችኋለሁ እና ልሰናበታችሁ።

የስለላ ድርጅቱ ወያኔና ሻዕቢያን ካርቱም ውስጥ በመጋበዝ (ካሁን በፊት ባቀረብኩት ሰነድ ውስጥ በወያኔ በኩል ስዩ፤ጻድቃን፤.... እንደነበሩ ዝረዝር ስም ጠቅሼ እንደነበር ይታወሳል) ዋና ዋና ንድፎቹ ግን የሚከተለውን ደርድሮች ነበሩ።

“1) በአሜሪካው ፕረዚደንት ስር የሚመራ ልዩ ቡድን ተመስርቶ በሱዳን አስቸኳይ የስራ ጉብኝት የሚያደርግ ቡድን ተቋቋመ።

ዋናው ተግባሩም፡ ህ.ግ.ሓ.ሔ እና ህወሓት በአካል በመገናኘት፡ በአሜሪካ መንግሥት የስትራተጂ እገዛ እየተደረገላቸው ሁለቱም ተባብረው የደረግን መንግሥት እንዲያስወግዱ ተነገራቸው። ከእገዛውም በከፊል፡ እንዲህ ያካትታል።

2) በሶቬት ሕብረት የተነደፈው የጦርነት ስትራተጂካዊ ሜላ በሳተላይት እየተጠለፈ ለህ.ግ.ሓ.ሔ. እና ለ ህ.ወ.ሓ.ት በምስጢር እንዲተላለፍ።

3) ኢትዮጵያ ያሉት ነባራ ጀነራሎችት ለመከታተል በከፊል ለስለላ እና ክትትል እንዲረዳ ህ.ግ.ሓ.ሔ. እና ለወያኔ ልዩ በጀት ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ፡፡ ጀኔራሎቹ እና አዋጊ ሃይሎቻቸውን (የደርግን) በገንዘብ ሓይል እንዲያዳክሟቸው ከዚያም በእውቅም በምስጢርም እንዲገደሉ ማድረግና እንዲመናመኑ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ፡ ያ በጀነራል መርእድ ንጉሴ እና በጀነራል ኣበበ አበራ

የተጠነሰሰው መፈንቅለ መንግስት እንዲከሽፍ ማድረግ፡፡ መጨረሻ ላይም፤ ታለላቅ አዋጊ መኮንኖቻቸውና አዛዦች እንዲሁም አዋጊ መሃንድሶቻቸው ከተገደሉ በኋላ፡ የቀይ ኮከብ ዘመቻ እንዲሰናከል ማድረግ፤ የሚሉ አሉባቸው።”

ምፅዋ ላይም፡- ውግያው በሳተላይት መረጃ እየታገዘ፤ እንዲሁም በደርግ ወታደራዊ አዛዦች ውስጥ ቀደም ብለው ለጠላት ያደሩ (ባንዳዎች) አማካይነት የሰራዊቱ ሞራል እንዲላሽቅ ማድረግ። የምፅዋን ወደብ እንድያዝ። በኋላ አስመራ ሻዕብያ እንዲቆጣጠረው፤ ኣዲስ ኣበባ ደግሞ ወያኔ እንዲቆጣጠረው። ኮለኔን መንግስቱ ሃይለማርያም በተቻለ መጠን ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ እንዲሸ እገዛ ማድረግ……ወዘተ። የሚሉ እንደሚገኙበት ከሻዕቢያ ራሳቸውን ያገለሉ ዛሬ ተቃወሚ የሆኑ ከፍተኛ የድርጅቱ ሰዎች ይፋ አድርገውታል። ዝርዝር መረጃው በራሴ ብሎግ (ኢትዮጵያን ሰማይ) ከ 3ት አመት በፊት ‘ቀይ ባሕር ላይ ያንጣለለው መጪው ጥቁር ዳመና’ በሚል የቀረበው ካንድ የሻዕቢያ ውስጥ አዋቂ የተገኘ ሰነድ ያቀረብኩትን ሰነድ ይመልከቱ። በተለየ ሰነድ ያቀረብኩት የምፅዋን ውድቀት ምክንያቶች ያልተከታተላችሁ ብትኖሩ በወታደሩ ውስጥ ተሰግስገው በከፍተኛ እርከን የኢትዮጵያ ወታደራዊ አዛዦች ቦታ ተመድበው፤ የተሰጣቸው አደራ ጥሰው የሻዕብያን ሴራ ከተባበሩት መካከል

የዓፋሩ ተወላጅ  ብርጋዴር ጀኔራል አሊ ሓጂ አብደላሂን በዚህ አጋጣሚ ላስታውሳችሁ እወዳለሁ። ሰውየው፤ ለውጭ አገር ጋዜጠኞች ቃለ መጠይቅ በሰጠበት ወቅት (ጦርነቱ እየተፋፋመ በነበረበት ወቅት ምፅዋ ላይ ለሻዕብያ እጁ በመሰጠት "ለ20 አመት ስዋጋ፤ ለምን ስዋጋ እንደነበር አላወቅኩም ነበር"፤ በማለት ደሞዝ እየተከፈለው ጀኔራል ደረስ ማዕረግ የደረሰ ሰውዬ ለምን ስዋጋ እንደነበር አላወቅኩም በማለት፤ ብሔራዊ ሉዓላዊ ድምበር እንደመናኛ ነገር በመቁጠር፤ ጦርነቱ አሁኑኑ ይቁም፤ወታደሩ እጁን ይስጥ፡ በማለት በጥሩ አንግሊዝኛው ለውጭ አገር ጋዘየጠኞች መልእክቱን እያስተላለፈ፤ ጸረ ኢትዮጵያ ቅስቀሳው ለማጠናከርም ሲዋጋ ለነበረው የኢትዮጵያ ሰራዊት ወታደራዊ እገዛና እርዳታ እንዳይደረግለት ተማጽኖ ነበር። የግዝገዛው ሴራ ዛሬም በተለያዩ አቅጣጫዎች በማህበራዊ ኑሮ፤ በፖለቲካዊ፤በጆኦግራፊያዊ፤ በመሬት ነጠቃ ፤በድምበር ረገጣና በሕዝባችን አንድነት፤በማንነተቻን፤ በጠቅላላ በሉአላዊነታችንና በክብራችን ላይ ጥቃቱ እየቀጠለ እንደሆነ ለመጠቆም እወዳለሁ። በአገራችን ህልውና ላይ በውጭ ሃይላትና በውስጥ ተባባሪዎቻቸው የሚሰነዙሩብን ሴራዎች ለማቆም በተቃዋሚ ቡድኖች እና በወያኔ ውስጥ የተሰገሰጉት "ባንዳዎች" የሚሰነዝሩት ቅስቀሳና ድርጊት በጥንቃቄ እንድታስተውሉት አሳስባለሁ። ኢትዮጵያ ለዛላም ትኑር! አመሰግናለሁ። ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ

(getachre@aol.com)     www.ethiopiansemay.blogspot.com

Ethiopian Semay